# የሱዳን ጦር የወረራ ዘመቻውን እያጠናከረ ነው
# <u>የወያኔ ድብቅ ሴራ እየተጋለጠ ነው</u>

**ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ**

**ግንቦት** 1 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** ( May 9, 2008 )

**የኢትዮጵያን ዳር ድንበር አሳልፎ በመስጠት የተለከፈው የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በድብቅ ስምምነት ለሱዳን አሳልፎ የሰጠውን ለምና ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ያለው መሬት በይፋ እንዳይጋለጥ የሚያደርገው መፍጨርጨር በሕዝቡ መጋለጡ እንደቀጠለ ነው። የሀገር ክህደት ድርጊቱ ኢትዮጵያውያንን እጅግ ከማስቆጣቱም በላይ ፤ ተቃውሞውም በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀጥሏል።**

**ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ድረስ እርዝመቱ** 1600 **ኪሎ ሜትርና የጎን ስፋቱ ከ**30 **እስከ** 50 **ኪሎ ሜትር የሚደርሰው ይህ እጅግ ለም መሬት በድብቅ አሳልፎ በመስጠት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ነው ብለን አንገምታለን። ይህ ለሱዳን ገጸ-በረከት የተሰጠው ለም መሬት በኢትዮጵያ ታሪክ ማሕደር ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የታሪክ ምዕራፍ የያዘ ነው። የኢትዮጵያ አንድነት አርማ የሆኑት አፄ ቴዎድሮስ ተወልደው ያደጉበትና የሀገር ዳር ድንበር ለማስከበር ከወራሪ ግብጾችና ቱርኮች ጋር የተፋለሙበት ፤ አፄ ዮሐንስ የወራሪው ድርቡሾች ( ሱዳን ተስፋፊዎች ) ጦር ለመከላከልና የኢትዮጵያን ነፃነትና ዳር ድንበር ለማስከበር በቆራጥ ጀግንነት መተማ ላይ የተሰውበት እንዲሁም አፄ ኃይለሥላሴና የኢትዮጵያ አርበኞች ከ**5 **ዓመት የኢጣሊያን ወረራ በኋላ የሱዳንን ድንበር አቋርጠው ኢትዮጵያ ምድር ሲደርሱ የነፃነታችን አርማ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ የተከሉበት አካባቢ ነው። ይህ ታሪካዊና ለም መሬት የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ባደረገው ምስጢራዊ ስምምነት መሠረት የሱዳን ጦር አካባቢውን ወሮ የኢትዮጵያውያንን ንብረት አቃጥሎ** 34 **ወገኖቻችንን አሥሮ ወስዶ በቦታው ላይ ቋሚ ጽሕፈት ቤት ከፍቶ ባለበት ወቅት ፤ መንግሥት ነኝ ባዩ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሕዝቡ ወረራውን እንዳይመክትና ከአካባቢው እንዲርቅ በአግአዚ ጦሩ አማካኝነት የሚያደርገውን ሴራ እጅግ ገፍቶበታል።**

**በኢትዮጵያ መሬት ላይ ጽሕፈት ቤት የከፈተችት የወራሪው ሱዳን ጦር ባለሥልጣናት የታሰሩት ኢትዮጵያውያንን « የሱዳን መሬት » አርሳችኋል በማለት እያንዳንዳቸው** $100,000.00 **( አንድ መቶ ሺህ ዶላር ) መክፈል አዳለባቸው ፣ ይህ ካልሆነ ግን እንደማይፈቱና ከ**10 **እስከ** 15 **ዓመት የሚደርስ እሥራት እንደሚፈረድባቸው አስታውቀዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ፤** 6 **ኢትዮጵያውያን እስረኞች እያንዳዳቸው** 50 **ጅራፍ መገረፋቸው በቅርቡ የደረሰን መረጃ ይገልጻል።**

**ይህ በዚህ እንዳለ ፤ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት በሱዳን ወረራ የተፈናቀሉ ወገኖቻችን ለተቃጠለው ንብረታችሁ ካሣ ገንዘብ እንዲሰጣችሁ ከፈለጋችሁ መሬቱ ለሱዳን መስጠቱንና በወረራ ስለደረሰው ጉዳት ለጋዜጣዎች ቃላችሁን እንዳትሰጡ እያለ ማስፈራራቱን ቀጥሏል። ነዋሪው ሕዝብ ግን ብሶቱን እየገለጸ ዳር ድንበሩን ለማስከበር ማንም ኃይል ሊያቆመው እንደማይችል በማረጋገጥ በዝግጅት ላይ ይገኛል።**

የሱዳን ጦር በአካሄደው ወረራ ወቅት 34 ወገኖቻችን ተይዘው ወደ ሱዳን ተወስደው መታሰራቸውንና በስቃይ ላይ መሆናቸውን የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው ከዚህ በፊት መግለጹ የሚታወስ ነው። የእነዚህ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ስም ዝርዝር ለማግኘት ባደረገነው ጥረት በአሁኑ ወቅት የ16 ሰዎች ስም ለማግኘት ችለናል። እነርሱም ፥

ሀ/ <u>ከአቶ አፍወርቅ የኋላአሸት የእርሻ ጣቢያ የተወሰዱ</u>

1ኛ/ አቶ ወርቂ ሽፈራው
2ኛ/ አቶ ማሩ ትኩየ
3ኛ/ አቶ ምስጋናው ሙሉ
4ኛ/ አቶ ገብሬ አዳነ
5ኛ/ አቶ ደረጀ ዓለሙ
6ኛ/ አቶ አብዱ አይደር
7ኛ/ ወ/ሮ ምጥን ዳኘው
8ኛ/ አቶ አራጋው

ለ/ <u>ከአቶ ፈንታሁን አሰፋ የእርሻ ጣቢያ የተወሰዱ</u>

ጠቅላላ ተይዘው የሄዱት 7 ሲሆኑ ፤ ስማቸውን ያገኘነው ግን የ4ቱን ብቻ ነው።
1ኛ/ አቶ ደምሌ
2ኛ/ አቶ ወርቁ
3ኛ/ አባ መላኩ
4ኛ/ አቶ ምስጋናው

ሐ/ <u>ከአቶ መሐሪ መብራህቱ የእርሻ ጣቢያ የተወሰዱ</u>

1ኛ/ አቶ መሐሪ መብራህቱ ( የእርሻው ጣቢያ ባለቤት )
2ኛ/ አቶ ኢድሪስ ሳልህ
3ኛ/ አቶ አሊ አብዲ
4ኛ/ አቶ አብድራሂም

በሌላ በኩል ደግሞ ፤ በውጭ ሀገር ኢትዮጵያውያንን እንወክላለን የሚሉ የወያኔ አምባሳደሮች የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ የሰጠውን የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የሀገር ክህደት ገመና ለመሸፈን በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሴራውን ለማጋለጥ የሚያደርጉትን ጥረት ለማስቆም ከንቱ ሙከራ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ከተለያዩ የዜና አውታሮች ጋር ቃለ-መጠይቅ የሚያካሂዱት የድንበር ኮሚቴ አባላትን በስልክ የማስፈራሪያ መልዕክት እንዲደርሳቸው እያደረጉ ነው።

## ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሆይ!

ይህ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ድንበሩን በተመለከተ የሚደረገውን ድብቅ ሴራ እየተከታተለ በማጋለጥ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው ፣ እንዲያወግዘውና እንዲታገለው ፤ እንዲሁም የዓለም ሕብረተሰብ እንዲረዳው በማድረግ ላይ ይገኛል። ኮሚቴው የተጣለበትን የዜግነት ግዴታ በተጠናከረ መልኩ ሊወጣው ይችል ዘንድ ፤ በአሁኑ ወቅት በሥሩ ልዩ ልዩ ዘርፎችን አቋቁሞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ይህ አሁን በከፍተኛ ደረጃ በተለያዩ ዘርፎች የተዋቀረው የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በቅርቡ ፥

1ኛ/ ታላቅ የተቃውም ሰላማዊ ሰልፎች ለማካሄድ ፤
2ኛ/ በየአካባቢው ሕዝባዊ ስብሰባዎች ለመጥራት ፤
3ኛ/ የአቤቱታ ፊርማ ማሰባሰቢያ ማመልከቻ ( Petition ) በዓለም-አቀፍ ደረጃ ለማስፈረምና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የዓለም መንግሥታትና አሕጉራዊ ድርጅቶች እንዲሁም ሀገሮች ለማቅረብ ፤
4ኛ/ ለዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት የሚቀርብ በታሪካዊ ጥናት የተደገፈ ሠነድ ለማዘጋጀት በመሆኑ ሁኔታዎችን በትጋትና በጥሞና እንድትከታተሉ እናሳስባለን።

በዚህ እጅግ አሳሳቢ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚችለው ሁሉ የሀገራችን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር በሚደረገው ከፍተኛ ጥረት ታሳታፊ እንዲሆን ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የፖለቲካ ድርጅቶች ፣ የሲቪክ ማህበራት ፣ የሃይማኖት ተቋማትና የንግድ ድርጅቶች በያሉበት የኢትዮጵያዊነት ግዴታቸውን እንዲወጡ ፤ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገሮች ማለትም በአፍሪካ ፣ በአውሮፓ ፣ በአሜሪካ ፣ በአውስትራሊያና በመካከለኛው ምሥራቅ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፤ በአህጉርም ሆነ በሀገር ደረጃ የአንድነት ድምጻችንን ለማሰማት ቅንብሩ ዓለም-አቀፍ እንዲሆን ከታች በተገለጸው ኢሜል ( e-mail ) አድራሻ ልታገኙን እንደምትችሉ በትህትና እንገልጻለን።

እንደተለመደው የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው የሁኔታዎችን እድገት በቅርብ በመከታተል ተከታታይ መግለጫዎችን የሚያወጣ መሆኑን እየገለጸ ፤ በተቃራኒው በኩል ግን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በዚህ እጅግ አሳሳቢ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ለመጨመር ወይም እንዲባዝን የሚያደርጉ ሁኔታዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ጥንቃቄ የሚያስፈልግ መሆኑ ከወዲሁ በጥብቅ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!

የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር የአባቶቻችን ቃል-ኪዳንና አደራ አለብን!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
ኢሜል አድራሻ/ E-mail: leethiopia@yahoo.com